# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**የከቲት 09 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የወያኔ ቡድን በሾማቸው ባለስልጣናት ላይ የምንጠራ ዘመቻ ጀመረ፤**

**በሙዋቹ መለስ ዜናዊ የወያኔ ታማኝ ተብለው የተሾሙ አምባሳደሮች ተንሳፈፉ፤**

**የአዲስ አበባ ከተማ በአንድ ከንቲባ በሶስት ምክትል ከንቲባ ልትመራ ነው ተባለ፤**

**አዲዮስ የአዲስ አበባ ከንቲባ የኦህዴዱ ኩማ ደመቅሳ ተሰናበተ፤**

**የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት አባላት ሲነታረኩና ሲወዛገቡ ሰነበቱ፤**

**የመከላከያ ቀን ተብሎ ከሕዝብ ካዝና በተደረገ ወጪ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የደረሰበት ጠፋ፤**

የወያኔ ዘረኛ ቡድን ለዓመታት ስርዓቱን በእግሩ እንዲቆም ሲታገሉ የነበሩትን ነባር ካድሬዎች በተለያዩ ሰበቦች ከስልጣናቸው እያንሳፈፋቸው መሆኑን ከተለያዩ ተቁዋማት የደረሱን ጥቆማዎች አጋለጡ፡፡

በኦህዴድ ባለስልጣናት ላይ ጥቃት ሲዘነዝር የነበረው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን በብአዴንና በቤንሻንጉል ክልል ባለስልጣናትም ላይ የጥቃት በትሩን ማሳረፍ መጀመሩን ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በተለይ በምእራብ ኢትዮጵያ በኩል የነበረውን ስጋት ሲያቃልሉ ነበር ተብለው በሙዋቹ መለስ ዜናዊ ሲሞገሱና ሲወደሱ የነበሩት የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባለስልጣናት አሁን ባሉት ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለስልጣናት ትዕዛዝ ከየክልሎቹ እንዲነሱ የተደረገ ሲሆን አንዳንዶቹን ወደ ዘብጥያ እያወረዱዋቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ሰሞኑን ከስልጣናቸው ከተነሱት የክልሉ ባለስልጣናት መሀከል የክልሉ አፈ ጉባኤ እና የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ የሚገኙበት ሲሆን ሌሎች የቢሮ ኃላፊዎችም ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ተገናኝታችሁዋል በሚል ከየስልጣናቸው መነሳታቸውን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል  አፈ ጉባኤ በመለስ ሲወደስ እና ሲሞካሽ የነበረ ቢሆንም በአሁኖቹ ባለስልጣናት ዘንድ ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ስውር ግንኙነት አላችሁ የሚል ታፔላ ተለጥፎባቸው እንዲባረሩ የተደረገ ከመሆኑም ባሻገር አንዳንዶቹን የአይናችሁ ቀለም አላማረንም በሚል ሰበብ ለእስር እንደዳረጉዋቸው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ሙስናን ይዋጋል ተብሎ የፌዴራል የጸረ ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ሆኖ የተሾመው አዲሱ የተባለው የብአዴን ሰው ደግሞ የህዝብ እና የሀገር ሀብት ዘርፎዋል በሚል ሰበብ ከስልጣኑ ተነስቶ በፍትህ ሚኒስትር በአንድ መምሪያ ውስጥ እንዲቀመጥ መደረጉም ታውቆዋል፡፡

ይህ ግለሰብ በብአዴን በኩል የኮታ ማሙያ ይሆናል ተብሎ ተቀመጦ የነበረ ቢሆንም በሕወሀቶች ዘንድ ቅሬታን በመፍጠሩ ከቦታው ላይ እንዲነሳ ተደርጎ በምትኩ የደቡብ ክልል የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበረው የወላይታው ተወላጅ ዋዶ አዶ  የተተካ ሲሆን በዋና ዳይሬክተርነት የመለስ ቅርብ ሰውና ምስጢር ጠባቂ የሆነው የወሎው ተወላጅ የብአዴኑ ሰው ሱሌይማን አሊ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ከሕወሀት  ካድሬዎች በስተቀር በሀገር ውስጥ እና በውጭ ያሉትን ባለስልጣናት  በያሉበት እያተራመሱቸው ከመሆኑም ባሻገር አንዳንዶቹን ከስልጣናቸው እያነሱ የሰዓት ፊርማ እንዲፈርሙ አድርገው እየተጫወቱባቸው እንደሚገኝም ታውቆዋል፡፡

ወደ ተለያዩ የዓለማት ክፍሎች ተበትነው የነበሩት አምባሳደሮች ሳይቀሩ በቅርቡ በተጀመረው ምንጠራ በትሩ ያረፈባቸው በመሆኑ ከ16 ያላነሱ አምባሳደሮች በረከት ስምኦን፤ አባይ ጸሀዬና ቲዎድሮስ አድሀኖም በሰጡት ትዕዛዝ ከተሾሙበት ሀገር ተጠርተው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቢሮ የሰዓት ፊርማ እያስፈረሙዋቸው እንደሚውሉ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

አንዳንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ አምባሳደሮቹ በአሁኑ ሰዓት በቁም እስር ላይ እንደሆኑና የቅርብ የደህንነት ክትትል እንደሚደረግባቸው ጠቁመው የዚህ ችግር ሰለባ የሆኑት ብዙዎቹ ደግሞ የኦህዴድ ሰዎች መሆናቸውን አጋልጠዋል፡፡

አምባሳደሮቹ የሀገሪቱን ሳይሆን የወያኔን አቋዋምና ጥቅም ለማስከበር ዘብ ቆመው የነበረ ቢሆንም ሲሰሩለት እና ሲደክሙለት የነበረው ዘረኛ ፓርቲ መልሶ ከተሰቀሉበት አውርዶ የፈጠፈጣቸው ከመሆኑም ባሻገር ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል በሚል ሰበብ ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ሳይመጡ በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ እና በቁም እስር እንዲሆኑ ተደርጎ እንደሚገኙ ጨምረው ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

የዘመኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆነው ቲዎድሮስ አድሀኖም በበኩሉ ወቅቱ የሰጠውን ስልጣን መከታ በማድረግ በአምባሳደሮቹ ላይ እየተዛበተ ሁሉም የራሳቸው ችግር ያለባቸው በመሆኑ ለግዜው አይመደቡም አስፈላጊ ከሆነም ለጥያቄ ይቀርባሉ እያለ መዘባነኑ ያንገበገባቸው እነኚሁ አምባሳደር ተብዬዎች አብዛኞቹ ተጠርተው ሳይመጡ የቀሩትን አስታውሰው እነሱ ጥሪ አክብረው በመምጣታቸው እየተቆጩ መሆኑንም ምንጮቹ ገልጸዋል።

ወደ ሀገር ውስጥ እንዲመለሱ ጥሪ ከተደረገላቸው 67 አምባሳደሮች መሀከል ከ35 የማይበልጡ የተገኙ ቢሆንም ከነዚህ መሀከል 18 አምባሳደሮች ሀገር ቤት ተቀምጠው ውሳኔያቸውን እንዲጠባበቁ ተብሎ ታግደው የነበረ ሲሆን ሁለቱ በአማላጆች እንደገና ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ተደርጎ 16ቱ እዚሁ እየታሹ እንደሚገኝ ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

ለስብሰባ ተጠርተው አንመጣም ያሉት አምባሳደሮች የወያኔ ትልቅ ቱባ በለስልጣናት እንደነበሩ ምንጮቹ ጠቁመው ከእነዚህ መሀከል የኦህዴዱ ባለስልጣናት በበዛት እንደሚገኙበት ታውቋል።

የኦህዴድ ባለስልጣናት በሕወሀት የበላይነት ጥብቅ ክትትል ስር በመሆናቸው ያበሳጫቸው በመሆኑ ለስብሰባም ሆነ ለኮርስ እንደማይመጡ ምክንያት የሰጡ ቢሆንም በእነ ቲዎድሮስ አድሀኖም በኩል ግን ባለመምጣታቸው ቁጣን ያስከተለ ስድብ ቀረሽ መልዕክት እንደደረሳቸው ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

መለስ ዜናዊ  ቀኝ እጅ ናቸው ተብለው ሲነገርላቸው የነበሩት የኦህዴድ ባለስልጣናት ሳይቀር እሱ ከሞተ ወዲህ በአሁኖቹ ሶስት ቁንጮ ባለስልጣናት ማለትም በበረከት ስምኦን፣በአባይ ጸሀዬ እና በቲዎድሮስ አድሀኖም ዘንድ ድጋፍ እና ይሁንታ ባለማግኘታቸው በያሉበት እየዋለሉና እየተንገዋለሉ መሆናቸውም እየተነገረ ይገኛል።

ሰሞኑንም ከወያኔ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነታቸው ህግና ደንቡ ከሚያዘውና ከሚፈቅደው ውጭ ተሰርዘው ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባልነት ለማስመረጥ እጩ ተደርገው በይፋ መነገሩ የአሁኖቹ ሶስቱ ሰዎች የወያኔ ባለስልጣናትን እኪሳቸው እንዳስቀመጡት ሳንቲም ቆጥረው እያሽከረከሩዋቸው መሆኑን ያረጋገጠ እውነታ ነው።

በሕዝብ ተመረጡ ተብሎ ሲለፈፍላቸው እንዳልነበር ለመረጣቸው ሕዝብ እና ክልል ሳይነገር ......የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ጭምር ሳይሰማ እንደ ባይተዋር ተቆጥሮ በድንገት በወያኔው የምርጫ ተጠሪ ሬድዋን ሁሴን በኩል ከምክር ቤት አባልነታቸው መወገዳቸው መሰማቱና ለአዲስ አበባ ምክር ቤት እጩ ሆነው መቅረባቸው መነገሩ የወያኔ ቡድን ውስጥ አሁንም ትልቅ ትርምስ መኖሩን የሚያመላክት ነው ተብሎዋል።

ሰሞኑን ከወያኔ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነታቸው ከተነሱት ከፍተኛ ባለስልጣናት መሀከል አንድ ኦህዴድ...ሁለት ደኢህዴኖች.....አንድ ህወሀት.....አንድ ብአዴን መሆናቸው የታወቀ ሲሆን እነሱም የደኢህዴን ኮታ የሆኑት የመከላከያ ሚኒስትሩ ሲራጅ ፈርጌሳ ....የኮንስትራክሽንና የከተማ

ልማት ሚኒስትሩ  መኩሪያ ሀይሌ...... የኦህዴዱ ኮታ ማሙያው የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጄኔራል ወርቅነህ ገበየሁ  ... መለስን በጥያቄ የስንግ ይዞ አላላውስ እንዳለው ሲነገርለት የነበረው የብአዴኑ የግብርና ሚኒስትሩ ተፈራ ደርበው......እንዲሁም የህወሀቱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስትር ሚኒስትር ደኤታው ዶ/ር አብርሀም ተከስተ መሆናቸው ታውቆዋል።

ከእነዚህ ውጭ ደግሞ ሁለት የክልል ስራ አስፈጻሚ የሆኑት  የኦህዴዱ የትራንስፖርት ሚኒስትሩ ድሪባ ኩማ እና የብአዴኑ የትራንስፖርት ሚኒስትሩ ሚኒስትር ደኤታው ጌታቸው መንግስቲ እንደሆኑም ታውቆዋል።

የሀገሪቱ ቁልፍ የሆነችውን አዲስ አበባ ከተማን ለመቆጣጠር በሚል አዲስ እቅድ በወያኔ ተነድፎ የቀረበ ሲሆን አሁን ላሉት ሶስቱ ሰዎች ሳይልኩዋቸው ወዴት ሳይጠሩዋቸው አቤት ሊሉ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸውን ሰዎች ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ከክልል ምክር ቤት አፈናቅለው አምጥተው ሰግስገው አዲስ መዋቅር ሊዘረጉ እንደሆነም ተነግሮዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያዋን በኦሮሚያ ክልል ስር የምትገኝ በመሆኑ ስልጣኑን ማለትም የከተማ ከንቲባነቱን  ለኦህዴድ ሰጥቶ ከስሩ ሁለት ወይም ሶስት ምክትል ከንቲባ መዋቅር ተዘርግቶ የብሔር ተዋጽኦ በሚል ህወሀት ደኢህዴንና ብአዴን የሆኑት ሶስቱ ባለስልጣናት ከስር እንዲሆኑና በጋራ እንዲሰሩ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት የኦህዴዱ የትራንስፖርት ሚኒስትሩ ድሪባ ኩማ ከሚኒስትርነቱ ተነስቶ በከንቲባነት ሲሾም ሌሎቹ ከሚኒስትርነት ስልጣናቸው ተነስተው የምክትል ከንቲባነት ቦታ የሚሰጣቸው ሲሆን የህወሀቱ ዶ/ር አብርሀም ተከስተ.. የብአዴኑ ተፈራ ደርበው እና የደኢህዴኑ መኩሪያ ኃይሌ ሊሆኑ ይችላል ተብሎ በስፋት እየተነገረ ሲሆን የተቀሩት ወርቅነህ ገበየሁ...ሲራጅ ፈርጌሳ...ጌታቸው መንግስቲ ደግሞ የአዲስ አበባ የምክር ቤት አባል ሆነው እንዲቀጥሉ ሲደረግ በምትካቸው ታማኝ የሆኑ የወያኔ አጎብዳጅ ወጣት ካድሬዎች ተፈልገው የሚኒስትርነቱን ስልጣን ይረከባሉ ተብሎም እየተነገረ ይገኛል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሕይወት እያለ ዋና እና ቀንደኛ ተቀናቃኝ ናቸው ብሎ ያሰባቸውን የህወሀት ሰዎች በአምባሳደርነት እና በጡረታ ስም  ካባረረ በሁዋላ ታማኝ እና ታዛዥ ናቸው ያላቸውን ወጣት እና ነባር ካድሬዎች በሚኒስትርነት ሾሞ ሲያሰራቸው ከነበሩት መሀከል የአዲስ አበባው ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ አንዱ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ ምክንያቶች ካሉት መሪዎች ጋር ባለመግባባቱ የተነሳ ከቦታው ተነስቶ መተካካት በሚለው ፈሊጥ ስርቻ ስር ሊወትፉት እየተዘጋጁ መሆኑንም ቅርበት ካላቸው ወገኖች የደረሰን ጥቆማ ያብራራል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የህወሀት ስጋት ነው እየተባለ በገዛ ካድሬዎቻቸው እየተነገረ የሚገኝለት ኦህዴድ በአዲስ አበባ ሲፋተግ ሰንብቶ እንደገና የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በሚል በአዳማ/ናዝሬት መሰንበቱ ታውቆዋል።

በአዳማ ገልማ አባገዳ አዳራሽ በተደረገው በዚሁ የምክር ቤት ስብሰባ ላይ በምክር ቤቱ አባሎች መሀከል ስምምነት ጠፍቶ እርስ በርስ ሲናቆሩ መሰንበታቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ካድሬዎቹን በአዲስ አበባ ዋናው የኦሮሚያ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ውስጥ በዝግ አፍኖ እርስ በርስ ሲያፋትጋቸው የነበረውና ከሞት የተረፈው የክልሉ ፕሬዝዳንት እና የኦህዴድ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ በድጋሚ በአዳማ የምክር ቤት ስብሰባ ላይ በመገኘት ስብሰባውን ሲመራ እንደነበርም ታውቀዋል፡፡

በምክር ቤቱ አባሎች መሀከል ትልቅ ልዩነት ፈጥሮ የነበረው የዳኞች ሹመት እንደነበር የስብሰባው ተሳታፊዎች ጠቁመው በተለይ አለማየሁ አቶምሳ ያለበት ቡድን ለወያኔ አጎብዳጅ እና ትራፊ ለቃሚ በመሆኑ የክልሉን ጥቅም የማያስከብር በመሆኑ እሱ መርጦ ለሹመት ያቀረባቸው ዳኞችም ተመሳሳይ በመሆናቸው አናጸድቅም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኖ ማለፉ ውዝግብ በማስነሳቱ ለሁለት ቀናት ሲያነታርካቸው እንደሰነበተ ታውቀዋል፡፡

በዚሁ ለቀናት በሰነበተው የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ሲያነታርክ እና ሲያወዛግብ የነበረው የዳኞች ሹመት ጉዳይ ጥቂት ማሻሻያ ተደርጎበት ከሁለት ቀናት ቆይታ በሁዋላ መልሶ እንዲጸድቅ መደረጉንም ከስብሰባው ተሳታፊዎች የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ሌላው የስብሰባው ዋነኛ መነጋገሪያ ሆኖ የነበረው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበረው ፍቃዱ ሰቦቃ በአሁኑ ሰዓት የኦሮሚያ ክልል የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ ሆኖ እየሰራ ስለሚገኝበት መስሪያ ቤት ሪፖርት እንዲያቀርብ ተብሎ የተዘበራረቀ ሀሳብ በማስደመጡ ከምክር ቤት አባሎች ክፉኛ ተቃውሞ እንደተስተጋባበት ከተሳታፊዎቹ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ግለሰቡ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በኦሮሚያ በሚነሱ ግጭቶችና መፍትሔዎቻቸው ዙሪያ ማብራሪያ ተጠይቆ መልስ ለመስጠት ተቸግሮ ከመታየቱም ባሻገር አጎራባች የሱማሌ ብሔረሰብ ተወላጆች ክልል ላይ የጥፋተኝነት ውንጀላ በማስደመጡ በምክር ቤቱ አባሎች ክፉኛ መተቸቱን የተሳታፊዎቹ ጥቆማ ጠቅሶ ፍቃዱ የተባለው ይሄው የኦህዴዱ ባለስልጣን በእኛ ምድር የሱማሌ ክልል ተወላጆች ቦታ አያገኙም የኦሮሚያን መሬትም አሳልፈን አንሰጥም እያለ በማስፈራራቱም የምክር ቤት አባሎች ተቃውሞ ከማሰማታቸውም ባሻገር በግለሰቡ ላይ ጠንካራ ትችት መሰንዘራቸው በስፍራው ከነበሩ ተሳታፊዎች የተገኘው ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

ምክር ቤቱ የኦሮሚያ ቲሊቪዥን ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ለብዙ ዓመታት የሰራውን ባለሙያና ከሰራተኛ ጋር ተግባብቶ የነበረውን ሰው ከቦታው አንስቶ የአዳማ ከንቲባ ሆኖ በቅርቡ የተሾመውን በክሪ ሻሊ የተባለውን ግለሰብ በበላይነት እንዲቆጣጠር ተብሎ የተወሰነ ቢሆንም ጋዜጠኞቹ ሙያ የሌለው ሰው ፖለቲካ እንጂ ስራ አያሰራንም በማለት ተቃውሞ እያሰሙ እንደሆነም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን በሰራዊቱ መሀከል ያለውን የእርስ በርስ ኩርፊያና የአንድ ወገን የበላይነት ነግሶዋል ጥያቄ ለማዳፈን ሲል ባዘጋጀው የመከላከያ ቀን በቢሊዮን የሚቆጠር የሀገሪቱን ገንዘብ እንዳባከነ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋለጠ፡፡

ከመክፈቻው የካቲት 1 ቀን እስከ መዝጊያው የካቲት 7 ቀን 2005 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ በተለያዩ ስፍራዎች በተደረገው የመከላከያ ቀን የበአል አከባበር ዝግጅት ላይ ከሕዝብ ካዝና በተደረገ ወጪ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የተበተነ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የሰራዊቱን ቁጣ ያበርድልናል ብለው ባዘጋጁት በዚሁ በዓል ላይ ከመስመራዊ መኮንኖች እስከ ከፍተኛ ቁንጮ መኮንኖች ድረስ የአንድ ወገን ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ብቻ የነበሩበት ከመሆኑም ባሻገር በአሁኑ ሰዓት በሰራዊቱ ውስጥ የተነሳውን ጥያቄ አጉልቶ ያሳየ ዝግጅት እንደነበረም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ከመከላከያ ኤታማዦር ሹሙ ሳሞራ የኑስ ጀምሮ እስከ ሻለቃ አዛዦች ድረስ የትግራይ ተወላጅ የህወሀት መኮንኖች ብቻ መሆናቸውን ያሳየውና ያጋለጠው የመከላከያ በዓል ላይ የይስሙላ ጠቅላይ ሚኒስትር የተባለው የደኢህዴኑ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሳይቀር እንደ ባይተዋርና የዳር ተመልካች ጥሪ ተደርጎለት ተንከርፍፎ መዋሉ የአንድ ወገን የበላይነት መንገሱን ያረጋገጠ ነው ተብለዋል፡፡

በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የህወሀት መኮንኖች ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ከመያዛቸውም ባሻገር የሲቪል ካድሬዎችን ጭምር እየተቆጣጠሩና እየመሩ መሆናቸውን ያሳየ በዓል እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ እስከ ሚኒስትሮች ድረስ ያሉ ባለስልጣናት ለህወሀት ጄነራል መኮንኖቹ እየተሽቆጠቆጡ አላስፈላጊ ሽር ጉድ ሲያደርጉ ለተመለከተ ትልቅ ትዝብት ላይ የጣላቸው መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት የጦር መኮንኖች የህወሀት ሰዎች መሆናቸውን ያጋለጡት ምንጮቹ ከእነዚህም መሀከል የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹሙ ጄኔራል ሳሞራ የኑስ... የሰሜን ዕዝ አዛዥ ሳዓረ መኮንን ..... የዳር ፉር የሰላም አስከባሪ ጦር ዋና አዛዥ ታደሰ ወረደ..... የምስራቅ እዝ አዛዥ አብርሀ ወ/ማርያም.....የመከላከያ የሎጀስቲክ ክፍል ኃላፊ ገዛኢ አበራ... የመከላከያ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኃላፊ ክንፈ ዳኘው.....የመከላከያ ኢንዶክትሪኔሽን እና ዶኩመንቴሽን ክፍል ኃላፊ ገብረኪዳን ገ/ማርያም..... በሱማሊያ የዘመተው ጦር ዋና አዛዥ ኃ/ጊዮርጊስ.....የአግአዚ ጦር ዋና አዛዥ መሀመድ አሳ እና ሌሎች ቁልፍ ሰዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ከክፍለ ጦር እስከ ሻለቃ ድረስ ያሉትን ቦታዎችም የህወሀት መኮንኖች ብቻ እንዲቆጣጠሩት በመደረጉ የአንድ ወገን የበላይነት ተረጋግጦ በይፋ የታየበት ነው ሲሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡